

# ፀጋዬ ህያው ነው

ከሙታን ጋር መኖር ስለተጠየፈ፣
ትልቁ ፀጋዬ እርሱም አኮረፈ፣
ቀለሙን ከደነ ደብተሩን አጠፈ፣
ወደ ህያዋን ሰፈር እኛን ትቶ አለፈ::

በናት አገር ፍቅር ልቡ ሲነድ፣
ነዲዱን በቅኔ ሲያነድ፣
ድንጋይ ላይ ውሀ ሲያፈስ፣
ድንጋይ ላይ ረጥብ ላይርስ፣
ኑሮን ለራሱ ሳይኖር፣
ለሰው ህይወት ለሰው ሲኖር፣
ለፍትህ ሲከራከር፣
ስለ አንድነት ሲያስተምር፣
የቴዎድሮስን ታሪክ ሲቆፍር፣
ያሉላን ገድል ሲዘክር፣
የምንይሊክን ሚስጥር ሲመረምር፣
የዋቆ የዋርካን ታሪክ ሲያስተምር፣
የታሪክ ባላ ሲተክል ማገር ሲማግር፣
አንዱን ሲያስር ሌላው ሲተረተር፣
በጎሰኞች አንጀቱ ሲያር፣
ቢሰለቸው ድንጋይ መውቀር፣
ጥሎን ሔደ ህያው ሰፈር፣
ሃብተ ጊዮርጊስን ሊያናግር፣
አባጅፋርን ሊያማክር፣
ላሉላ የቀይ ባህርን የሞት መርዶ ሊነግር፣
ጥሎን ሄደ ወደ ህያዋን ሰፈር::

አዎን ፀጋዬ ህያው ነው፣
አሁንም ህያውያን ሰፈር ነው ያለው::

ከነገብርዬ ከነአብዲሳ ከነገልሞ፣
ከነአሊቢራህ ሃይለማርያም ማሞ፣
ህያው ታሪክ ከሰሩት፣
ላገር ቤዛ ከሆኑት ፣
ኢትዮጵያን  ኢትዮጵያ ካደረግዋት፣
አድዋ ላይ ከውርደት ካዳኗዋት፣
ማንነታቸውን ዶጋሊ ላይ ካሳዩት፣
አጋዴን ከወደቁት ፣
ከሙታን ተራ ወጥተው ህያው ሰፈር ከሚኖሩት::

ከሙታን ጋር መኖር ስለተጠየፈ፣
ትልቁ ፀጋዬ እርሱም አኮረፈ፣
ቀለሙን ከደነ ደብተሩን አጠፈ፣
ወደ ህያዋን ሰፈር እኛን ጥሎ አለፈ::

ቢገፉን ቢመቱን ህመም የማይሰማን፣
መብታችን ሲረገጥ ደንታ የማይሰጠን፣
በጠራራ ፀሃይ በጥይት ተቆልቶ ሲያልቅ ወገናችን፣
ከኖረበት ቀዬ እየተነቀለ ሲጣል ወገናችን፣
ድንበሩ ተቆርሶ ማህሉ ዳር ሲሆን፣
አገር በጠቅላላ አቆፋዶ ይዞ አለምን ሲለምን፣

ይህ የማይቆጨን፣
ይህ የማይሰማን፣
ሙታኖች እኛ ነን፣
ፀጋዬ ህያው ነው!!

ከበአሉ ግርማ ብርሀኑ ዘሪሁን ፣
ከወጋየሁና ከመይሳው ጋራ መቅደላ ነው ያለው::

የቅኔው ማእበል፣
የቀለሙ ቀንዲል፣
የተውኔቱ መድብል፣
ብላቴን ጌታ ሎሬት ፀጋዬ አሁንም ህያው ነው!!!

አዲስ ከዳላስ